# “ሁሉም ለፍትህ የታገለ ያች የአደራ ቃል ማስታወስ አለበት!”

## ስዬ አብርሃ

-----------------------------------



*የኢትዮጵያ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ላለፉት ስድስት አመታት ታስረው የቆዩትን የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር አባልና የኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስቴር ሆነው ያገለገሉት አቶ ስዬ አብርሃ የታሰሩበት ጊዜ ከተፈረደባቸው ጊዜ በላይ ነው በማለት በነፃ አሰናብቷቸዋል። የቪኦኤ ትግርኛ ዝግጅት ክፍል ባልደረባ የሆነው ጋዜጠኛ በትረ ስልጣን አቶ ስዬ አብርሃን አነጋግሮአቸዋል።*

ቪኦኤ - አቶ ስዬ አብርሃ፣ ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ደስ ያልዎት እላለሁ!

አቶ ስዬ - አሜን፣ ያክብርልኝ።

ቪኦኤ - ከእስር ቤት እንደወጡ ጥቂት ቀናቶች ተቆጥረዋል። በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ቢገልፁልኝ?

ስዬ - ከቤተሰቦቼ ጋር ተገናኝቻለሁ። አሮጊት እናቴም በህይወትዋ አግኝቻታለሁ። መፈታቴ የሰሙ ወዳጆቼ ደስታቸውን እየገለጡልኝ ናቸው። በአገር ውስጥ፣ ከውጭ አገር፣ ምንም ዘር ሳይለይ ከሁሉም ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ የእንኳን ደስ ያለህ መልእክቶች ደርሰውኝ ደስ ብሎኛል።

ቪኦኤ- ስለ እናትዎ ክፉኛ መታመም የሚጠቁሙ ሪፖርቶች ነበሩ። አሁን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?

ስዬ - ደክማለች። ሁሉም ልጆችዋ በመታሰራችን ሃዘኑ በርትቶባት፣ እኛ እስርቤት እያለን እንዳትሞት፣ ለኛም ለስዋም በመሪር ሃዘንና በማይሽር ቁስል እንዳንለያይ እጅጉን እንሰጋ ነበር። የእግዜር ፈቃድ ሆኖ እግኝቻት፣ እስዋም ደስ ብሏት እስክ ሌሊቱ ስድስት ስዓት ስትጫወት በመቆየትዋ ገርሞኛል።

ቪኦኤ - ልጆችዎና ባለቤትዎስ እንዴት አገኝዋቸው?

ስዬ - ባለቤቴ በትግል ሜዳ እያለሁ ነው የተጋባነው። እስዋም እንደኔ በትግል ሜዳ ነበረች። እኛ ትዳር መስርተን ልጆች ወልደን ለማየት ዕድል አግኝተናል። እግዜር ምስጋና ይድረሰውና። ብዙ ጓደኞቻችን ይህን ዕድል ሳያገኙ በሞት የተለዩን እያሌ ናቸው።

እኔ ትግል ሜዳ ውስጥ በመግባቴ አባቴ ደርግ ገደለው። ወንድሜም ደርግ ገደለው። ወንድሞቼ ከኔ ጋር ትግሉን ተቀላቀሉ። ትንንሾቹ ደግሞ ያላሳዳጊ ተበትነው አደጉ። ከኔ አልፎ ለልጆቼ፣ ለአሰፋ (አብርሃ) ልጆች፣ ለፍስሃ (አብርሃ) ልጆች፣ ለምህረተአብ (አብርሃ) ልጆች አዳርሷል። የደረሰብን ፈተና እጅግ ለማሰብ የሚያስቸግር ከባድ ነበር።

ይሁን እንጂ በወገን ብርታት፡ ሞራላቸው እንደተጠበቀ ነው ያገኘሁዋቸው።

ቪኦኤ - እስርቤት በቆዩበት ወቅት ምን አይነት ተሞክሮ ቀስመው እንደወጡ ባጭሩ ቢያስረዱኝ።

ስዬ - መከራ ነው። ግን መከራ ደግሞ ያስተምራል። 17 ዓመት ሙሉ ጦርነት ላይ ቆይተን ብዙ ትምህርት ተምረን ነበር። በዚሁ ላይ ስድስት አመት እስራት ተጨምሮበት ሌላ የህይወት ግንዛቤ አስጨብጦኛል።

ባለፈው የትግል ጊዜ እንዲሁ ሩጫ ነበር። እየተደናበሩ የሚሮጡበት ጊዜ ነበር። ረጋ ተብሎ፣ ቆም ተብሎ፣ ከራስ ጋር የሚተዋወቁበት፣ መጪው ጊዜ ደግሞ ምን እንደሚመስል በአይነ ህሊና የሚቃኙበት ጊዜ አልነበረም። ምንም እንኳ መታሰሬ ችግር ላይ ቢጥለኛም፣ ቁጭ ብዬ ከራሴ ጋር ለመመካከር፣ ያለፈው የትግል ጉዞ ምን ይመስል እንደነበር ለመቃኘት፣ መጪው ጊዜ ደግሞ ምን እንደሚሆን፣ በአእምሮዬ ለማብሰልሰል ጊዜ፣ ሁኔታዎችንና አቅሙንም ፈጥሮልኛል።

እኔ መታሰሬን አመካኝቼ እያማረርኩኝ፣ እየተራገምኩኝ አይደለም ስድስቱን አመታት ያሳለፍኩት። እያሰብኩና ከራሴ ጋር እየተማከርኩኝ ነው ያሳለፍኩት። አቅሜን እያጎለበትኩኝ ነው ያሳለፍኩት።

ቪኦኤ - ወደ ኋላ ልመልስዎትና እርስዎ በስልጣን ላይ እያሉ በኢህአዴግ መንግስት በኩል ተፈፅመዋል የሚልዋቸው ስህተቶች ነበሩ ወይ?

ስዬ - ጥያቄው ሰፋት ያለው ነው። ዛሬ ጎድኟል የምንለው ራሱ መልስ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ እንኳ በአገሪቱ ያለው ሁኔታ ካየን ፍትህ የለም። ነፃ ዳኝነት ብሎ ነገር የለም። ነፃ ፕሬስ የለም። ፍርሃት፣ ስጋት፣ መቃቃር የመሳሰሉት ችግሮች ያያለፈው ጉዞ የወለዳቸው ችግሮች አሉ።

ቪኦኤ - ባለፈው ቃለ-መጠይቅ ላይ ሲናገሩ ህገ-መንግስቱንና የዳኞች ነፃነት መከበር አለበት ብለው ነበር። መንግስት ደግሞ የፍርድ ቤቶችና የዳኞች ነፃነት እንዳለ ነው የሚገልፀው። ይህ እንዴት ያዩታል?

ስዬ - ከንግግር በላይ ተግባር በይበልጥ ያናገራል። ህዝቡ ደግሞ ዋናውና ትልቁ የአይን ምስክር ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ የዳኝነት ነፃነት እንዲኖር ምን ይደረግ ነው ማለት ያለብን እንጂ እጆቻችን አጣጥፈን የፍርድ ነፃነት አለ ብሎ እሰጥ-አገባ ማለቱ የትም የሚያደርስ አይመስለኝም።

ቪኦኤ - እስር ቤት እያሉ የ97ቱ ምርጫ ተካሄደ። ግሚሱ ተቃዋሚ ፓርላማ ሲገባ፣ ግሚሱ ደግሞ አንገባም ብለው፣ ሁከት ተቀስቅሶ፣ በአሁኑ ሰዓት የቅንጅት መሪዎች በእስር ላይ ይገኛሉ። ስለዚህ ምን አስተያየት አልዎት?

ስዬ - በቴሌቪዥን ያየሁትንና በሬድዮ የዳመጥኩትን ብቻ በማገናዘብ ነው እንግዲህ አስተያየቴን ለመስጠት የምሞክረው። በምርጫው ወቅት ሰፊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ተስተውሏል። ብዙ ተዋንያን መድረክ ላይ ወጥተው ነበር። ምናልባትም ግዙፍ የፖለቲካ ንቃት ተከስቶ ነበር ማለት ይቻላል። ልክ የእግር ኳስ አፍቃሪ በሙሉ ማንችስተር ዩናይትድ፣ አርሰነል ወዘተ እያለ በፍቅር እንደሚከታተል ሁሉ፣ በእኛ አገርም ሁሉ ሰው ስለ ፖለቲካ የሚናገርበት፣ ስለ አገራችን መፃኢ ዕድል ምን መሆን እንዳለበት የሚወያይበት ጊዜ ሆኖ ታይቷል። በዚህ እንግዳ ሂደት ውስጥ ችግሮች፣ ጉድለቶች ከሁሉም ወገን ሊታዩ እንዲሚችሉ ሊገመት ይቻል ነበር።

ነገር ግን በነዚያ ችግሮችና ድክመቶች ተስፋ ሳንቆርጥ ሂደቱን ጠብቀን ብንከተለው ኖሮ በአገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ትልቅ አዎንታዊ እንደምታ ይኖረው ነበር ባይ ነኝ። ቀደም ብሎ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ አሰራር ቢታከልበት ኖሮ በኢትዮጵያ የፖሊቲካ ታሪክ፣ በኢትዮጵያ የተሃድሶ ፖለቲካ

እጅግ ትልቅ ምዕራፍ ሊከፍት በቻለ ነበር። ለነዛ ለፍትህ ብለን ጠመንጃ አንስተን ለታገልን ለጮህን እጃችንን ላወጣን ሰዎች ደግሞ ትልቅ የህሊና እረፍት በሆነልን ነበር። አለመታደል ሆነና አጨራረሱ እንደዚያ ሊሆን አልቻለም። ሰዎች ታሰሩ። ህይወት ጠፋ። ያሳዝናል።

አሁንም ቢሆን ምንም እንኳ ብዙ ጉዳት ቢደርስም ለማረም ዕድል የለም ማለት አይደለም። አሁንም ቢሆን ለአገር ሲባል፣ ለህዝብ ሲባል፣ ለሰላም ሲባል ሆደ-ሰፊ ሆኖ በትዕግስት ተወያይቶ ጉዳዩ እልባት እንዳያገኝ በሩ ዝግ ነው የምልበት ምክንያት የለም።

<u>ቪኦኤ</u> - መፃኢ የአገሪቱ የፖለቲካ ህይወት እንዴት መቀጠል አለበት ይላሉ?

<u>ስዬ</u> - ይች አገር ብዙ ችግር ያሳለፈች አገር ናት። ኃያል፣ ጠንካራ፣ የማትበጠስ፣ ተስፋ የማትቆርጥ አገር ነች።  ጦርነት፣ ረሃብና ችግር የማይፈታው ህዝብ ያደላት አገር ነች። በዚህ ልዩ ፀጋ ላይ ተሞርክዘህ ልንሰራ፣ ተመካክረን ለህዝብ ለአገርና ለመጪው ትውልድ ሲባል ተቀራርበን ስጥና ውሰድ (give and take) ተባብለን ተመካክረን መስራት ይኖርብናል እላለሁ። ስጥና ውሰድ ሊኖር ከሆነ ደግሞ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መደረክ ላይ መታየት (መተግበር) ይኖርበታል እላለሁ።

<u>ቪኦኤ</u> - ወደ ሌላ ጥያቄ ልውሰድዎት። እርስዎ በስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ በኤርትራና በኢትዮጵያ የድንበር ውዝግብ ምክንያት ምንም እንኳ የድንበር ኮምሽን የመጨረሻ ያለውን ውሳኔ ቢያሳልፉም ችግሩ እርስዎ እንደትዉት ነው። ድንበሩ አለተከለለም። ዛሬ ወደ ኋላ መለስ ብለው ሲያዩት ያ ጦርነት መነሳት ነበረበት ይላሉ?

<u>ስዬ</u> - እንደኔ ከሆነ ኤርትራና ኢትዮጵያ ከተለያዩ በኋላ የኤርትራ ጉድለት ጎልቶ የወጣ ይመስለኛል። የኢትዮጵያ ጎድለትም ጎልቶ የወጣ ይመስለኛል። ወንድማማችነት፣ አብሮ መስራት፣ ሰላም ፍትህና ዴሞክራሲ እንደ ድልድይ ሆነው ባልተገነቡበት ወቅት የኤርትራና የኢትዮጵያ መለያየቱ ነገሮችን ያባባሰ ይመስለኛል። ሩጠን፣ ሩጠን፣ ተካኩሰን፣ ተታኩሰን ምን እንዳገኘን፤ የ30ና የ40 አመት ተጋድሎ ውጤቱ ምን እንደሆነ በአይናችን እያየነው ያለ ይመስለኛል።

እንደኔ አመለካከት ከሆነ ችግራችን ባድመ ላይ አይደለም ያለው። ችግራችን ያ ሊያስተሳስረን የነበረ፣ ያ ሊያስተባብረን የነበረ ገመድ መበጠሱ ነው። ያ የፈተና ወቅት እንደምንም አልፈነዋል። ያ ቁስል ግን ለልጆቻችን፣ ለልጅ ልጆቻችን ጠስ እንዳይሆን አርቆ ማስተዋል፣ ቆም ብለን ረጋ ብለን እንደገና መሰብ፤ ያ በኤርትራ ያለው ችግር፣ ያ በኢትዮጵያ ያለው ችግር በአንድ መነፅር ውስጥ አስገብተን ማየት መቻል አለብን። እርስ በርስ ከመናቆር፣  ኤርትራ ውስጥ ያለውን ችግር፣ ኤርትራ ውስጥ ያለው የነፃነት እጦት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውም ችግር አስወግደን የህዝብ መብት የተከበረበት መድረክ ከፈጠርን፣ ልጆቻችን ደግሞ ከኛ በተሻለ ኑሮአቸውን ለማስተካከል ዕድል ሰጠናቸዋል ማለት ይመስለኛል።

<u>ቪኦኤ</u> - እሺ። የእርስዎስ መጪው የፖለቲካ ሕይወትዎ ምን ሊመስል ይችላል። ወደ ፖለቲካ ይመለሳሉ ወይስ ፖለቲካ ይተውታል?

<u>ስዬ</u> - ድሮ ልጅ እያለሁ የወሰንኩት ውሳኔ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሬ ረዥም መንገድ ተጉዣለሁ። አምሳ አመት ያሳለፍኩ ሽበቶ ነኝ። ከአሁን በኋላ ወደኋላ መመለስ የሚቻል አይመስለኝም። ያሁሉ አደራ፣ ያሁሉ ጀግና የተሰዉበት ዓላማ ትተን ዛሬ በስተርጅና ላይ ልንከዳቸው አንችልም። ስለዚህ የትግሉ አካሄድ፣ ስልቱና ስትራተጂው ይቀየር እንደሆን ነው እንጂ፣ እኔ ከፖለቲካ እወጣለሁ ማለት እነኛ እኔን የሚያውቁኝ ሰዎችም ጭራሽ ያልሙታል አልልም።

ቪኦኤ - አቶ ስዩ ለአድማጮች የሚያስተላልፉት ተጨማሪ መልእክት ካለ?

ስዩ - አገራችን ከባድ ችግር ላይ ትገኛለች። ይህ ሸክም ትልቅ ነው። በእኔ እና በቤተሰቦቼ ላይ የደረሰ ግፍ ደግሞ አለ። እሱም ትልቅ ሸክም ነው። ሁለቱን ተሸክሜ ልዘልቀው አልችልም። አንዱን መምረጥ አለብኝ። ስመርጥ ደግሞ እኔ የከፋኝ ይከፋኝ እንጂ፣ ለአገሬ ለህዝቤ ሊጠቅም የምችለውን ነው መምረጥ የመፈልገው። ስለሆነም ተፈትቻለሁ። እምነቴ ደግሞ ፅኑ እንደሆነ አውቃለሁ። እኔን የሚያውቅ ሰው ደግሞ በጥላቻና በብቀላ የምመራ ሰው እንዳልሆኑኩኝ ያውቃል። የኔ ፍላጎት ለወደፊቱ ለአገር በሚጠቅም፣ ለህዝብ በሚጠቅም ጉዳይ ላይ ጊዜየን ማጥፋት የምመኘው።

የመቀሌ ህዝብ የአባቴን አጥንት ለቅሞ ሲቀበር እዛው እመቃብሩ ላይ የገባነው ቃል ፅፌን ትተን ነበር። በምንም መልኩ ህዝቡ እንዳይበደልና የሚያኮራ ስራ ሰርተን በታሪክ ማለፍ ብለን ነበር። ሌላው ቃል የገባነው ዓዲ ሓቂ (መቀሌ ውስጥ) ባለው የሰማዕታት ሃወልት ላይ በእብነበረድ የተቀረፀ የእምነት ቃል አስፍረን ነበር። በማንኛውም መልኩ ግፍ እንደማንቀበል፣ በማንኛውም ህዝብ ላይ ግፍ እንዲፈፀም እንደማንቀበል፣ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል በደል እንዲፈፀም እንደማንፈቅድ በተሰዉት ሰማዕታት ስም ቃል ገብተናል። ደም ሲፈስ ዝም ካልን የቺ የገባንባት ቃል አላከበርንም ማለት ነው ተባብለን ነበር። ሁሉም ለፍትህ፣ ለሓቅ የታገለ ያች የአደራ ቃል ማክበር ይጠበቅበታል።

ቪኦኤ - አቶ ስዩ አብርሃ ለሰጡን ማብራርያ ከልብ አመሰግናለሁ።

ስዩ - እሺ የኔ ወንድም።

---

**አቶ ስዩ አብርሃ ከአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ የትግርኛው ዝግጅት ክፍል ጋር ያደረጉትን ቃለ-መጠይቅ ወደ አማርኛ ተርጉመው ለዝግጅት ክፍላችን የላኩልን የጋሻ ለኢትዮጵያውያን ሲቪክ ማህበር አባላትን እናመሰግናለን። - ኢትዮሚድያ**

www.ethiomedia.com